# የዲሲ ዲኤምቪ ለተወሰኑ ጉዳዮች የሚያገለግል ማስረጃ ሂደት(ፕሮሰስ)

**በሜይ 1፣ 2014 ዲሲ የተሽከርካሪዎች ዲፓርትምንት(ዲኤምቪ) (DC Department of Motor Vehicles (DMV) ) ለተወሰኑ ጉዳዮች የሚያገለግሉ የመንጃ ፈቃድ እና ለተወሰኑ ጉዳዮች የሚያገለግሉ የመታወቂያ ወረቀት (Limited Purpose Driver License and Limited Purpose Identification Card) ማተም (መስጠት) ጀምሯል።** ለዲሲ የተወሰነ ጉዳዮች የሚያገለግል ማረጋገጫ ሲያመለክቱ የተወሰነ ጉዳዮች የሚያገለግል ማረጋገጫ የአንድ ግዜ የሚደረግ የመረጃውን ምንጭ ሰነዶች መቅረብን ይጠይቃል። ለተወሰኑ ጉዳዮች የሚያገለግል መንጃ ፈቃድ ለሚያመለክቱ ሁሉም አመልካቾች የነጅው የእውቀት እና የጎዳና ላይ ፈተናዎች ግዴታ ነው። ለመጀመሪያ ግዜ የሚያመለክቱ የዲሲ ነዋሪዎች ቢያንስ ለ 6 ወራት በዲሲ ውስጥ ነዋሪ መሆን አለባቸው። አመልካቾች የሶሻል ሴኪሪቲ ቁጥር ኖሯቸው(ታትሞላቸው) የማያውቅ፣ ቀደም ሲል የሶሻል ሴኪሪቲ ቁጥር ታትሞላቸው የነበር ነገር ግን ከዚያ በሃላ ብቁ ያልሆኑ፣ ወይም ለሶሻል ሴኪሪቲ ቁጥር ብቁ ያልሆኑ መሆን አለባቸው። የተወሰነው ጉዳዮች የሚያገለግል ማረጋገጫው ለይፋ የፌዴራል አገልግሎት ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም እናም ይህንን መስፈርት ለመጠቆም ምልክት ይደረግበታል። ለተወሰኑ ጉዳዮች የሚያገለግሉ የመንጃ ፈቃድ ወይም የመታወቂያ ወረቀት ለማግኘት ቀጠሮ ማስያዝ አለቦት። ለተወሰነ ጉዳዮች የሚያገለግል የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት የዲኤምቪ (DMV) ቀጠሮዎ ቀን በፊት ለእውቀት ፈተናው እንዲዘጋጁ የመንዳት ማንዋሉን ማጥናቶን እና ማየቶን ያረጋግጡ። የእውቀት ፈተናውን ከወደቁ ሌላ ቀጠሮ እንዲወስዱ ይጠየቃሉ። ቀጠሮዎች በኦንላይን(በኢንተርኔት) መያዝ ይችላሉ እናም የአራቱ የአገልግሎት ማእከሎቻችን ሰአታት እና አድራሻዎች በድህረገጻችን dmv.dc.gov ወይም በ 311 (ወይም በ 202-737-4404) በመደወል ይገኛል።

**<u>ለተወሰኑ ጉዳዮች የሚያገለግሉ የመታወቂያ ወረቶች ለማግኘት የሚደረጉት የሂደት ደረጃዎች</u>**

**ደረጃ 1:** የማንነቶን ማረጋገጫ ማሰባሰብ፣ የሶሻል ሴኪሪቲ ቁጥር (SSN) ብቁ ያለመሆንን ቅጹን መሙላት፣ እታች ከተዘረዘረው መሀከል በአሁኑ ወቅት የዲሲ ነዋሪ መሆንን ማረጋገጥ እና ለ6-ወር ዲሲ ነዋሪ መሆንን ማረጋገጥ

**ደረጃ 2:** ለተወሰነ ጉዳዮች የሚያገለግል መታወቂያ ወረቀት ቀጠሮ በድህረገጻችን ላይ dmv.dc.gov ወይም በስልክ በ 311 (ወይም 202-737-4404) በመደወል ከዲሲ ዲኤምቪ ጋር መያዝ

**ደረጃ 3:** በቀጠሮዎ ቀን እና ሰአት የሚያስፈልገውን ሰነድ በሙሉ ጋር እና $20 የመታወቂያ ክፍያ ይዘው አግባብ ባለው የዲኤምቪ ስፍራ(አድራሻ) መገኘት

**<u>ለተወሰኑ ጉዳዮች የሚያገለግሉ የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት የሚደረጉት የሂደት ደረጃዎች</u>**

**ደረጃ 1:** የማንነቶን ማረጋገጫ ማሰባሰብ፣ የሶሻል ሴኪሪቲ ቁጥር (SSN) ብቁ ያለመሆንን ቅጹን መሙላት፣ እታች ከተዘረዘረው መሀከል በአሁኑ ወቅት የዲሲ ነዋሪ መሆንን ማረጋገጥ እና ለ6-ወር ዲሲ ነዋሪ መሆንን ማረጋገጥ

**ደረጃ 2:** ለተወሰነ ጉዳዮች ለሚያገለግል መንጃ ፈቃድ ቀጠሮ በድህረገጻችን ላይ dmv.dc.gov ወይም በ 311 (ወይም 202-737-4404) በመደወል ከዲሲ ዲኤምቪ ጋር መያዝ

**ደረጃ 3:** የእውቀት ፈተናውን ለመውሰድ ለመዘጋጀት የመንገዶችን ደንቦች ለመማር የመንዳት ማንዋሉን(ማጥኛ መጽሀፉን) ማጥናት (የሚገኝበት በኦንላይን dmv.dc.gov)

**ደረጃ 4:** በቀጠሮዎ ቀን እና ሰአት ከሚያስፈልገውን ሰነድ በሙሉ ጋር፣ እና $10 የእውቀት ፈተና ክፍያ እና $20 የለማጅ ፈቃድ ክፍያ ይዘው አግባብ ባለው የዲኤምቪ ስፍራ(አድራሻ) መገኘት

**ደረጃ 5:** የእውቀት ፈተናውን ካላለፉት ሌላ ቀጠሮ ከዲሲ ዲኤምቪ መውሰድ አለቦት። የእውቀት ፈተናውን ካለፉ፣ የለማጅ ፈቃድ ይሰጦታል።

**ደረጃ 6**: የለማጅ ፈቃዶን ካገኙ በሃላ፣ የጎዳና ላይ ፈተና ቀጠሮን በኦንላይን በ dmv.dc.gov ይያዙ።

**ደረጃ 7**: ለጎዳና ላይ ፈተናው ለመዘጋጀት፣ እድሜያቸው ቢያንስ 21 አመት ከሆነ ፈቃድ ያላቸው ነጂ ከርሶ አጠገብ የተሳፋሪ ወንበር ላይ ሆነው ባሉበት ፣የጎዳና ላይ መንዳትን መለማመድ።

**ደረጃ 8**: በጎዳና ላይ ፈተናው ቀጠሮ ቀን እና ሰአት፣ በትክክል የተመዘገበ እና ኢንሹራንስ ያለው ተሽከርካሪ እና ቢያንስ እድሜው 21 አመት የሆነው ፈቃድ ያለው ነጂ ጋር ሆነው በብሬንትውድ የጎዳና ፈተና ጣብያችን ( Brentwood Road Test Center) ይገኙ። $10 የጎዳና ላይ ፈተና ክፍያ፣ እና ለመንጃ ፈቃድ የ $44 ክፍያ ወይም ከ 21 አመት በታች ለሆኑ $20 የመሸጋገሪያ ፈቃድ ክፍያ አለው።

**ደረጃ 9**: የጎዳና ላይ ፈተናውን ካላለፉት ሌላ የጎዳና ላይ ፈተና ቀጠሮ መውሰድ አለቦት። የጎዳና ላይ ፈተናውን ካለፉ የመንጃ ፈቃዶን ያገኛሉ። (ማስታወሻ: እድሜዎ ከ 21 አመት በታች ከሆነ፣ ቀስ በቀስ ወደ አዋቂ ነጂዎች ማደጊያ ፕሮግራም (Gradual Rearing of Adult Drivers (GRAD) Program) ውስጥ ይገባሉ።)



የታረመበት 8/14/15

# የዲሲ ዲኤምቪ ለተወሰኑ ጉዳዮች የሚያገለግል ማስረጃ ሂደት(ፕሮሰስ)

***የማንነት ማረጋገጫ – ሙሉ ህጋዊ ስም እና የትውልድ ቀን***

**ከታች ከተዘረዘሩት መሀከል አንዱ(1) የመረጃው ምንጭ ማስረጃ ሰነድ ዋናውን(ፎቶኮፒ ያልሆነ) ማምጣት አለቦት:**

- ቀኑ ያልተቃጠለ ፓስፖርት
- የኮንሱላር ካርድ
- የዮኤስ የተረጋገጠ(ሰርትፋይድ) የትውልድ ምስክር ወረቀት(በርዝ ሰርተፍኬት) ወይም በስቴት ቫይታል ኦፍስ ኦፍ ስታትስቲክስ (State Office of Vital Statistics) የተመዘገበ የትውልድ የመስክር ወረቀት (በርዝ ሰርተፍኬሽን) ካርድ
- *ከፍርድ ቤት አገልግሎቶች እና የጥፋተኛ ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ(Court Services and Offender Supervision Agency (CSOSA))ወይም ከዲሲ ማረሚያ ቤት ዲፓርትመንት(DC Department of Corrections) የተሰጠ ስም እና የትውልድ ቀንን የሚያረጋግጥ፣ ፎቶግራፍ ያለው ደብዳቤ (መታወቂያ ወረቀትን ለማግኘት ብቻ የሚጠቅም)።

***ወይም***

**ከታች ከተዘረዘሩት መሀከል ሁለቱ (2) የሁለተኛ ደረጃ የመረጃው ምንጭ(secondary source) ሰነዶች ማምጣት አለበት እናም ዋናው(ኦሪጂናል) መሆን አለበት፡**

- የውጭ አገር የትውልድ ምስክር ወረቀት (ዋናው (ኦሪጅናል) ወይም የተረጋገጠ(ሰርትፋይድ) ኮፒ)
- ቀኑ ያልተቃጠለ የውጭ አገር የመንጃ ፈቃድ ወይም የመታወቂያ ወረቀት
- ቀኑ ያልተቃጠለ የዩናይትድ ስቴትስ የጦር ሀይል ወይም የጥገኛ የመታወቅያ ወረቀት
- የተረጋገጠ(ሰርቲፋይድ) የትምህርት ማስረጃ(ሪከርድ)

በእንግሊዘኛ ቋንቋ ያልሆነ ከውጭ አገር የሆነ የመረጃ ምንጭ ሰነድ ከሆነ ያሎት፣ የእንግሊዘኛውን ትርጉም ከኢምባሲዎ ወይም ማረጋገጫ ካለው (ሰርቲፋይድ ከሆነ) አስተርጓሚ ማያያዝ አለቦት።

***ለሶሻል ሴኪሪቲ ቁጥር ብቁ አለመሆንን ማረጋገጫ***

ለተወሰኑ ጎዳዮች የሚያገለግል የመንጃ ፈቃድ ወይም ለተወሰኑ ጉዳዮች የሚያገለግል የመታወቂያ ወረቀት የሚያመለክቱ ግለሰብ፣ የሶሻል ሴኪሪቲ ቁጥር ያልተመደበሎት መሆኑን፣ የሶሻል ሴኪሪቲ ቁጥር ተመድቦሎት ኖሮ ነገር ግን ማመልከቻውን ባቀረቡበት ግዜ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ህጋዊ ሆነው እንደቆዩ ሊያረጋግጡ እንደማይችሉ፣ ወይም የሶሻል ሴኪሪቲ ቁጥር ለመቀበል ብቁ እንዳልሆኑ የሶሳል ሴኪሪቲ ቁጥር ማረጋገጫ ቅጹ ላይ ማረጋገጥ አለባቸው። የሶሻል ሴኪሪቲ ቁጥሩ ማረጋገጫው ቅጹ (SSN Declaration Form) በኦንላይን(ኢንተርኔት) ይገኛል ወይም ለተወሰኑ ጉዳዮች የሚያገለግል ማረጋገጫዎ ቀጠሮ ሲመጡ ይገኛል።

*በአሁኑ ወቅት የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ነዋሪ መሆንን ማረጋገጫ*

**ከታች ከተዘረዘሩት መሀከል ሁለቱን(2) ማቅረብ አለቦት፣ ዋናው(ኦሪጂናል) መሆን አለበት (ለኦንላይን መክፈያዎች(ቢል) ከኮምፒውተር ፕሪንት የተደረገ መሆን ይችላል) እና ትክክል የሆነ የዲሲ አድራሻ ሊኖረው ይገባል (ፖስታ ሳጥን ተቀባይነት የለውም):**

- ባለፉት 60 ቀናት ውስጥ የታተመ ስምና አድራሻ ያለው የመጠቀሚያ(ዩቲሊቲ) መክፈያ (ውሀ፣ ጋዝ፣ ኤሌክትሪክ፣ ዘይት ወይም ኬብል)፣ (የማስቆረጫ ማሳሰቢያ/መክፈያ ወረቀት ተቀባይነት የላቸውም።)
- ባለፉት ስልሳ (60) ቀናት ውስጥ የታተመ የአመልካችን ስም እና በአሁኑ ወቅት ያሉበትን አድራሻ የሚያሳይ የስልክ መክፈያ (የእጅ ስልክ፣ ገመድ-አልባ(ዋየርለስ) ወይም የፔጀር ክፍያ ተቀባይነት አለው) (የማስቆረጫ ማሳሰቢያ/መክፈያ ወረቀት ተቀባይነት የላቸውም።)
- ባለፉት ስልሳ (60) ቀናት ውስጥ የታተመ የአመልካቹን ስም እና የንብረቱን አድራሻ የሚያሳይ የባለቤትነት ደብተር(deed)፣ ሞርጌጅ ወይም የስምምነት ወረቀት
- የአመልካቹ ስም እንደ ሊዚ፣ የተፈቀደለት ነዋሪ ወይም ተከራይ ሆኖ የተጠቀሰበት ቀኑ ያልተቃጠለ ሊዝ ወይም የኪራይ ስምምነት (ፎቶኮፒ ግልባጭ ሊሆን ይችላል)
- ማረጋገጫ አቅራቢው እንደ የተከራይ-ተከራይ(ሰብ ሊዚ) ሆኖ ያለበት ቀኑ ካልተቃጠለ ከዋናው የኪራይ ውል(ሊዝ) ጋር የተያያዘ፣ ቀኑ ያልተቃጠለ የተከራይ ተከራይ ውል(ሰብ ሊዝ)
- ባለፉት አስራ ሁለት(12) ወራት ውስጥ የታተመ የአመልካቹን ስም እና የንብረቱን አድራሻ የሚያሳይ የዲሲ የንብረት ግብር መክፈያ(ቢል)
- ስም እና አድራሻ የሚያሳይ ቀኑ ያልተቃጠለ የቤት ባለቤትነት ወይም የተከራይ ኢንሹራንስ ፖሊሲ

# የዲሲ ዲኤምቪ ለተወሰኑ ጉዳዮች የሚያገለግል ማስረጃ ሂደት(ፕሮሰስ)

- **ባለፉት ስልሳ (60) ቀናት ውስጥ የታተመ ስምን እና የዲሲ ነዋሪነትን የሚያረጋግጥ ከፍርድ ቤት አገልግሎቶች እና የጥፋተኛ ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ (Court Services and Offender Supervision (CSOSA)) ወይም ከዲሲ ማረሚያ ቤቶች ዲፓርትመንት (DC Department of Corrections(DC DOC)) የተሰጠ ፎቶግራፍ ያለው ደብዳቤ፣
- እቤት ውስጥ በሚኖሩ ወላጅ/አሳዳጊ ሞግዚት የተፈረመ እድሚያቸው ከ 21 አመት በታች ለሆኑ የዲሲ ዲኤምቪ የነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ (DC DMV Proof of Residency Certification Form For Residents Under Age 21) እና የወላጅ/አሳዳጊ ሞግዚት ቀኑ ያልተቃጠለበት የዲሲ የመንጃ ፈቃድ ወይም የዲሲ መታወቂያ ወረቀት ኮፒ እና በወላጁ/አሳዳጊው ስም የሆነ **2** የነዋሪነት ማረጋገጫ ሰነዶች (ማለትም፣ የመጠቀሚያ(ዩቲሊቲ) መክፈያ፣ የስልክ መክፈያ፣ ወዘተ)
- ከውጭ አገር ለመጡ ሞግዚት( Au Pair) የዲሲ ዲኤምቪ የነዋሪነት ማረጋገጫ
- ስም እና አድራሻ የሚያሳይ ባለፈው ስልሳ (60) ቀናት ውስጥ የታተመ የባንክ/ክሬዲት ካርድ/ኢንቨስትመንት ደብተር ዝርዝር (ስቴትመንት)
- የይፋ(ኦፊሻል) ፖስታ - ባለፈው ስልሳ (60) ቀናት ውስጥ ከዲሲ ዲኤምቪ ውጪ ከሆነ **ከማንኛውም** የመንግስት ኤጀንሲ የደረሶት (ሙሉ ስም እና አድራሻ ያለው) እንዲሁም ፖስታውን እና ውስጡ ተደርጎ የተላከውን የሚያካትት(የፖስታ አገልግሎት የአድራሻ ለውጥን ማሳሰቢያ ተቀባይነት **የለውም።**)
- *እውቅና ካለው የሶሻል ሰርቪስ አገልግሎት ሰጪ(Certified Social Service Provider) የተሰጠ እና የዲሲ ዲኤምቪ (DC DMV) ያጸደቀው ቅጽ
- ስም እና አድራሻ ያለው ባለፉት 60 ቀናት ውስጥ የተሰጠ የህክምና መክፈያ(ሜዲካል ቢል)
- ስም እና አድራሻ ያለው ባለፉት 60 ቀናት ውስጥ የተሰጠ የተማሪ ብድር ዝርዝር(ስቱደንት ሎን ስቴትመንት)
- ስም እና አድራሻ ያለው ባለፉት 60 ቀናት ውስጥ የተሰጠ የቤት ኢኪቲ ብድር ዝርዝር(ሆም ላይን ኦፍ ኢኪቲ ስቴትመንት)
- ስም እና አድራሻ ያለው ባለፉት 60 ቀናት ውስጥ የተሰጠ የመኪና/የግል ብድር ዝርዝር(ስቴትመንት)(የኩፖን ደብተር/ቫውቸር ተቀባይነት የለውም)
- ስም እና አድራሻ ያለው ባለፉት 60 ቀናት ውስጥ የተሰጠ የቤት ደህንነት ሲስተም መክፈያ(ሆም ሴኪሪቲ ሲስተም ቢል)

*የመታወቂያ ወረቀት ለማግኘት ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል እና ሁለተኛ የነዋሪነት ምንጭ አያስፈልገውም

ለ6-ወር በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ ነዋሪነትን ማረጋገጫ

የመረጃው ምንጭ ሰነድ(**ሁለት** ያስፈልጋል) **-** ቀኑ የዲሲ ዲኤምቪ ማመልከቻ ከገባበት ቀን አንስቶ ወደሃለ ሲቆጠር ቢያንስ 6(ስድስት) ወር በፊት የሆነ መሆን አለበት፣ ዋናው(ኦሪጂናል) መሆን አለበት(ለኦንላይን መክፈያ ከኮምፒተር የታተመ(ፕሪንት የተደረገ) ሊሆን ይችላል) **እና** ትክክል የሆነ የዲሲ አድራሻ ሊኖረው ይገባል(የፖስታ ሳጥን ተቀባይነት የለውም)፡

- "በወቅቱ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የነዋሪነት ማረጋገጫ" እንደሚያስፈልገው አንድ አይነት ማስረጃ ሰነዶች፣ ነገር ግን ቀኑ ከዲሲ ዲኤምቪ ማመልከቻው ወደሃላ ሲቆጠር ካለው 6(ስድስት) ወር በፊት መሆን **አለበት።**



የታረመበት 8/14/15